# የኦጋዴን ኢትዮጵያዊነት ።

ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ

January 1, 2018

ምእራፍ ሁለት
(ካለፈው የቀጠለ)

የኦጋዴን ሕዝብ እንደሌላው የሶማሌ ሕዝብ በቅኝ ገዥዎች የተገዛ ለመሆኑ የታሪክ ማስረጃ የለም፡፡ ቢሆንም አረቦች ወይንም ቱርኮች የሶማሌውን የባሕር ዳርቻ ለብዙ ዓመታት ሲገዙት የኦጋዴን ሕዝብና መሬት በባዕዳን ሳይደፈር ቆይቷል፡፡

እንዲህም ስለተባለ ቅኝ ገዢዎች ወይንም ተስፋፊዎችና ሰላዮች ሀገሩን አልረገጡትም ማለት አይደለም፡፡ የጣሊያን፣ የእንግሊዝና የፈረንሳይ ተስፋፊዎች ሀገሩ ውስጥ እየገቡ ወጥተዋል፡፡ ነገር ግን የቅኝ ግዛት ማስፋፋት ምኞች ያላቸው ሁሉ ተደጋግመው ስለተሙቱ ምኞታቸው ከሽፏል፡፡ በኢጣሊያዊው ኮንቲ ፓሮ ይመራ የነበረው ሚሲዮን በ 1885 በኦጋዴን ውስጥ ሲዘዋወር ከኦጋዴኖቹ በተጣለበት አደጋ መደምሰሱ ለዚህ ዓይነተኛ ማስረጃ ነው፡፡ ስለዚህ ኦጋዴኖች እንደሌላው የሶማሌ ጐሳ መሬታቸውን ለባዕድ አሳልፈው በገንዘብ ያልሸጡ ወይንም በብልጭልጭ ስጦታዎች ተታልለው ሀገራቸውን አሳልፈው ለባዕድ በውሉ ያላሲያዙ ወይንም ያላስተላለፉ በመሆናቸው በታሪካቸው ስለሚኮሩ ከሶማሌው ዘር ሁሉ የበላይነት የሚሰማቸው አግባብ መሆኑን ማስተባበል አይቻልም፡፡
የኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባር(ONLF) በሰጠው መግለጫ ግን ኦጋዴን በታሪከም፣ በፖለቲካም የኢትዮጵያ አካል ሆኖ እንደማያውቅ ይነግረናል፡፡

“The struggle of the people of Ogaden and the aim of their movement is to obtain the right of self determination rather than a struggle aimed at realizing of the identity of the nationalities. This is because Ogaden has never historically been part of Ethiopia (ONLF, 2004)”
በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የኦጋዴን ሕዝብ የተጣለበትን ግብር ለመንግሥት እየከፈለ ኢትዮጵያዊነቱን አምኖና ተቀብሎ በሠላም ከመኖር በቀር የባዕድ አገዛዝ መጣብኝ ብሎ አንዳችም እንቅስቃሴ አላደረገም፡፡

በዘመኑ የነበሩ የኢትዮጵያ አስተዳዳሪዎችም ፀጥታ ለመቆጣጠርና ግብር ለመሰብሰብ በቂ ጦር እያስከተሉ በዓመት ወይም በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ አገሩን በመጐብኘት ይቆጣጠሩት ነበር እንጂ፣ እንደዛሬው ዘመን ቋሚ አስተዳደርና ቋሚ ፀጥታ አስከባሪ ኃይል በማስፈር በቀጥታ አይቆጣጠሩም ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የሀገሩን ፀጥታ በመጠበቅና የሀገሩን ዳር ድንበር በማስከበር ደረጃ ኃላፊነቱ ለኦጋዴኖች የተተወ ስለሆነ የራስ-ገዝ(ኦቶኖሚ) አስተዳደርና መብት ተጐናፅፈው ነበር፡፡
የኦጋዴን አውራጃ በራሳቸወ በኦጋዴኖች እየተጠበቀ ከቆየ በኋላ የጣሊያን ቅኝ ገዢዎች መስፋፋት እንደገና ሲያገረሽ ቁጥጥሩን ለማጥበቅ ሲባል በ 1922 ለመጀመሪያ ጊዜ ደገሐቡርን የሚያስተዳድር ዳኛ በመንግስት ተሾመ፡፡ ቀጥሎም በ 1923 ሙስታሂልን፣ ቀብሪዳህርን ደናንንና ደገሃመዶን የሚያስተዳድሩ ገዢዎችና ፀጥታውንም የሚያስጠብቁ ኃይሎች ስለተመደቡ የኦጋዴን አገዛዝ እንደ ድሮው በተዘዋዋሪ መሆኑ ቁርቶ ከሞላ ጐደል በቀጥተኛና ቋሚ በሆነ አስተዳደር ተተካ፡፡ በወቅቱ በኦጋዴንና በጣሊያንና በእንግሊዝ አስተዳደር ሥር በነበሩት በሶማሌላንድ መካከል ያለው የወሰን ክርክር ከፍተኛ ችግር መፍጠር ጀመረ፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት እስከ 1922 ድረስ ኦጋዴንን በስም ከመያዙ በቀር ቀጥታ የሆነ አስተዳደር በኦጋዴን አልዘረጋም፡፡ ከ 1922 ጀምሮ በኦጋዴን ውስጥ በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ የአስተዳደር ዳኞች ቢመደቡም የኢትዮጵያ አስተዳደር በኦጋዴን መኖሩን ለማሳወቅ ያህል እረዳ እንጂ የተመደቡት አስተዳዳሪዎች አገልግሎት ሰጪዎች አልነበሩም፡፡ ያም ሆኖ ኦጋዴኖች

የኢትዮጵያ ዜጐች በመሆናቸው ብቻና ለባላባቶቻቸው አልፎ አልፎ ከመንግሥት በሚሰጠው የማዕረግ ስምና ሽልማት በመርካት ኢትዮጵያዊነታቸውን በስሜታዊ ፍቅር የተቀበሉ ናቸው፡፡

አጋዴኖች የኢትዮጵያ አስተዳደር ለማወቅ በቂ የጊዜ እድል ሳያገኙ ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ስለወረረች ከ 1928 እስከ 1933 ድረስ አምስት ዓመታት በኢጣሊያ ቅኝ አስተዳደር ሥር ወድቀዋል፡፡ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ምክንያት ፋሽስት ኢጣሊያ ድል ስትሆን የኢጣሊያንን አስተዳደር የተካው የእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡ የእንግሊዝ ወታደራዊ አስትዳደር "ከሪዘርቭድ ኤሪያ" በቀር የኦጋዴንን መሀል ሀገር ለኢትዮጵያ እስካስረከበበት ጊዜ ማለትም ከ 1933 እስከ 1940 ድረስ ኦጋዴኖች ለሰባት ዓመታት በእንግሊዝ መንግሥት አስተዳደር ቆይተዋል፡፡ የእንግሊዝ አስተዳደር "ከሪዘርቭድ ኤሪያ" ውስጥ የቆየበትን ጊዜ አቆይተን እስኪዚህ ጊዜ ድረስ ኦጋዴኖች በባዕድ አገዛዝ ሥር የቆዩበትን ዘመን ብናሰላው አስራ ሁለት ዓመታት ያህል ይሆናል፡፡

እስከ ኢጣሊያ ወረራ 1928 ድረስ ኦጋዴን የኢትዮጵያ አካል ሆኖ በኢትዮጵያ አስተዳደር ውስጥ ቢቆይም አስተዳደሩ የራስ-ገዝ ጠባይ የነበረውና ሕዝቡም ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት ዘመን ነበር፡፡ ስለዚህ የእንግሊዝ አስተዳደር በ 1941 ከመሀል ኦጋዴን ተነቅሎ የኢትዮጵያ አስተዳደር እንደገና ሲተካ ኦጋዴኖች ከጨቆናቸው አገዛዝ በመላቀቃቸው የኢትዮጵያን አስተዳደር የተቀበሉት በቀድሞው ስሜታዊ ፍቅራቸው ነበር፡፡ እንግዲህ መደበኛ የሆነ የኢትዮጵያ አስተዳደር በኦጋዴን ውስጥ ተቋቋመ ማለት የሚቻለው እንግሊዞች መሀል ኦጋዴንን ለቅቀው ከወጡ በኋላ በ 1941 ነው፡፡ ከዚህ ዘመን በኋላ በኦጋዴን ውስጥ ከአውራጃ እስከ ወረዳ የአስተዳደር መዋቅር ያልተዘረጋበት፣ የፖሊስ ጣቢያ ያልተቋቋመበት ክፍል አልነበረም፡፡ ይህም ዘመን የኢትዮጵያ መንግስት አስተዳደርና የኦጋዴኖች ቀጥታ የሆነ ግንኙነት የፈጠሩበት ፣ እንዱ ሌላውን ሊያውቅ የቻለበት የአዲስ ዘመን መከፈቻ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያ ጦር ዳኖት ላይ አመፀኞች በከበቡበት ጊዜ የተከበበው ጦር እርዳታ ወይንም መሣሪያና ስንቅ እንዳይደርሰው ለማድረግ ከዳኖት ጋር የሚያገኙትን የመገናኛ መንገዶች ዘግተው መንገዱን ሁሉ በቁጥጥራቸው ሥር አድርገውት ነበር፡፡ በደገሀቡር አውራጃ ውስጥ የሚተዳደሩት ሬርኢሣቅ የሚባሉ የኦጋዴን ጐሳዎች በአጋጣሚ ከዳኖት 20 እና 40 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ኢዶአና መሳሬ ከሚባሉት ቀበሌዎች ለግጦሽ ተሰማርተው ይገኙ ስለነበረ በኢትዮጵያ ጦር ላይ አደጋ መጣሉን እንደሰሙ ወደ ዳኖት በመገስገስ ከአመፀኞቹ ጋር ተዋግተው፣ የተዘጋውን መንገድ አስከፍተው፣ ከአመፀኞቹ ወገን 8 ሰው ገድለው አንድ ሲያቆስሉ 5 ጠመንጃዎች ማርከዋል፡፡ እንዲሁም 1300 ግመሎች 600 በግና ፍየሎች ማርከዋል፡፡ ከኦጋዴኖች ወገን ግን ሁለት ሰው ሲሞትባቸው ሦስት ሰዎች ብቻ ቆስለውባቸዋል፡፡ በተጨማሪም አጋዥ ጦር ዳኖት መድረስ የቻለው መንገዱን ኦጋዴኖች ካስከፈቱት በኋላ ስለነበረ ኦጋዴኖች በዳኖት ግጭት ላይ የተጫወቱት ሚና ለተገኘው ድል ወሳኝ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ከዳኖት ግጭት ቀደም ብሎ ታኅሳስ 5 ቀን 1953 በነጀኔራል መንግሥቱ ነዋይ አማካኝነት አዲስ አበባ ላይ የመንፈቅለ መንግሥስት ሙከራ መደረጉ ይታወሳል፡፡ በዚያን ጊዜ በዳኖት ላይ የተጣለውን ዓይነት አደጋ በሶማሊያ መንግሥት በኦጋዴን ውስጥ በየጦሩ ሰፈር አደጋ ያስጥላል የሚል መረጃ ስለሚጐርፍ ስጋት አሳድሮ ነበር፡፡ ይህንን ምክንያት በማድረግ በቀብሪደሀር አውራጃ የሚተዳደሩ የሬር አብደላ ኦጋዴን ጐሳዎች "በሕይወታችን እያለን የሀገራችን ዳር ድንበር አይደፈርም" በማለት፣ መንግስት በፈለገው መስመርና ግንባር እንዲያሰማራቸው በመጠየቅ 500 ፈረሰኞችና ከ 3000 የማያንሱ ከጠመንጃ እስከ ጦር ድረስ የታጠቁ የኦጋዴን ተዋጊዎች ቆራሄ ላይ አሰልፈው የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ በተጠንቀቅ እየጠበቁ ነበሩ፡፡ ሥጋቱ እያደር እየተቃለለ ስለሄደ መንግሥት እስኪጠራቸው ድረስ የተሰበሰበው ጦር ወደ የመንደሩ ይመለስ ተብሎ ስለተነገራቸው ኢትዮጵያዊነታቸውን አስመስክረውና በጐ ፍቃዳቸውን አሳይተው ተመልሰዋል፡፡

ኦጋዴኖች በዳኖት ግጭት ላይ በቀጥታ ተካፋይ ሆነው በመገኘታቸውና ቆራሄ ላይምየ መንግሥትን ለመደገፍ ጦር በማከማቸታቸው የሶማሊያ የገዢ መደቦች በፕሮፖጋንዳ መሣሪያዎቻቸው አማካይነት "ማተብ ያሰሩ አማሮች" ብለው አውግዘዋቸዋል፡፡

ኦጋዴኖች ግን ከሞቃዲሾ በሚጐርፈው ፕሮፖጋንዳ ለሶማሊያ መሪዎች ዓላማና ፍላጐት አልተበገሩም፡፡ እንዲያውም ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የበለጠ መቀራረብና መተባበር እየመሠረቱ መሄዳቸውን የተገነዘቡት የሞቃደሾ ባለሥልጣኖች

ሁኔታው በጣም ያሳሰባቸው ጀመር፡፡ አንዳንድ የሶማሊያ የጐሣ መሪዎችም በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ የሚታየውን ቸልታና እንዲህ ያለውን የኦጋዴኖች ደካማ ጐን በመገንዘብ "ኢትዮጵያዊነታችንን አንለቅም ብላችሁ ሙዝዝ ብትሉም ከአማራ ተገዢነት አልወጣችሁም፡፡ አማሮቹ የነፈጓችሁን የሥራና የትምህርት ዕድል፣ እንዲሁም መተዳደሪያ እኛ ወገኖቻችሁ እንሰጣችኋላን" በማለት ብሶታቸውን የሚያባብስ ፕሮፖጋንዳ ከማሠራጨት ችላ ያሉበት ጊዜ አልነበረም፡፡
በዚህም ሰበብ አንዳንድ የኦጋዴን ባለሀብቶች የሀገር ሽማግሌዎች ከተማረው ወጣትም መሀል አንዳንዶች እየኮበለሉ ወደሞቃዲሾው መሄድ ጀመሩ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የኦጋዴኖች መኮብለልና በስብከት መማረክ የሞቃዲሾው መንግሥት ቶሎ ይደርሳል ብሎ ሳያስብና ሳይዘጋጅ የሆነ ነገር ስለሆነ ኮብልለው የሄዱት የሚበዙት ኦጋዴኖች ሞቃዲሾ ከደረሱ በኋላ በፕሮፖጋንዳው የሰሙትን ሊያገኙ ይቅርና ዞር ብሎ የሚያያቸው እንኳን አጥተው በየከተማው በችግር ስለማቀቁ የኢትዮጵያን መንግሥት ይቅርታ በመጠየቅ ተመልሰው ወደሀገራቸው የመጡ ይገኙባቸው ነበር፡፡

ይህ ሁኔታ ለኢትዮጵያ ታማኝ የሆኑትን ከፍሎች የሚያደፋፍር ሆኖ ስለተገኘ ወደሞቃዲሾው በኮበለሉትና ከዚያው በቀሩት ባላባቶች ምትክ የኦጋዴን ሕዝብ በምትካቸው አዲስ ባላባቶች እየመረጠ ይሾራቸው ጀመር፡፡ ከዚህም በላይ የኦጋዴን ሕዝብ ከመንግሥት ጋር በመተባበር በአንድ ወገን የኢትዮጵያንና የራሱን ጠላቶች በፖለቲካ ሜዳ ሲዋጋ በሌላ ወገን ደግሞ ከነበረው ሥርዓት ጋር ስለኢትዮጵያዊነት ሙብቱ ይታገል ነበር፡፡

ወልወል
የእንግሊዝና የኢትዮጵያ መንግሥስት የወሰን ክለላ ሥራ መልዕክተኞች በእንግሊዝ ሶማሌላንድና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን ወሰን በ 1897 ስምምነት መሠረት በ 1931 የተጀመረውን የወሰን ክለላ ሥራ ተካልለው ከጨረሱ በኋላ የእንግሊዝ ጥገኛ ሶማሌዎች በዝናቡ ወቅት ከፕሮቴክቶሬቱ ግዛት ወደ ኢትዮጵያ (ኦጋዴን) እየገቡ ከብቶቻቸውን ሣር ለማስጋጥ የሚችሉበትን የግጦሽ ክልል የሆነ መሬት ለመወሰን በኦጋዴን ውስጥ ከሥፍራ ሥፍራ እየተዘዋወሩ የጥናት ሥራ ያከናውኑ ነበር፡፡ ይህ የጋራ ኮሚሽን የጥናቱን ሥራ በማከናወን ላይ እያለ የኢጣሊያ መንግሥት ጦር ወሰን አልፎ መጥቶ፣ ወልወል ላይ ሰፍሮ በመገኘቱ ሁኔታው እስኪጣራ ድረስ በአቅራቢያው ከሚገኘው አዶ ከሚባል ሥፍራ ሰፍሮ ነበር፡፡ ይሁንና ኮሚሽኑን ያጅብ የነበረው የኢትየጵያ ጦር የኢጣሊያንን ጦር ወሰን አልፎ የገባበትን ምክንያት ለማጣራትና ቢቻልም በሠላማዊ መንገድ ተነጋግሮ ለማስወጣት ወልወል ላይ ሠፈረ፡፡

የኢጣሊያ ጦር አዛዥ የኢትዮጵያ ጦር ከወልወል ውሃ እንኳን ቀድቶ እንዳይጠቀም ከመከልከሉ ሌላ "ያለሁት በግዛቴ ላይ ነው ፡፡ ወሰንም አላለፍኩም፡፡ ይልቁንስ ወሰን አልፋችሁ የመጣችሁት እናንተ ስለሆናችሁ ከዚህ ነቅላችሁ ሂዱልን" ብሎ የዛቻ መልስ ሰጠ፡፡ በዚህ ጊዜ ሁኔታው ተባብሶና መታረቅ ከማይቻልበት ደረጃ ደርሶ በጣም ስለተካረረ ለጦርነት መነሻ ምክንያት ሊሆን ቻለ፡፡ የመጀመያው የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ግጭት በወልወል ላይ በታኅሳስ ወር 1934 ተጫረ፡፡
ፋሺስቱ ሙሶሊኒ የአድዋን ሽንፈት የምንበቀልበት አጋጣሚው ጊዜ አሁን ነው ብሉ የደነፋውም ይህን ግጭት አስመልክቶ ነበር፡፡ የቀድሞው የዓለም ማኅበር (ሊግ ኦፍ ኔሽን) አባል መንግሥታትም ለሙሶሊኒ ድንፋታ ተንበረከኩ፡፡ ኢትዮጵያም አሳልፋው በወራሪው ሃይል እንድትጋለጥ አደረጓት፡፡ ስለሆነም በዘመናዊ ትጥቅ፣ ማለትም በታንክና በአውሮፕላን ጭምር በዳበረው በኢጣሊያ ወራሪ ጦርና ለጦርነት ባልተዘጋጀው፣ ከወኔ በቀር በቂ መሣሪያ ባልታጠቀው የኢትዮጵያ ሠራዊት መካከል በመላው ኦጋዴን በጥቅምት ወር 1935 ጦርነቱ ተቀጣጠለ፡፡ በዋቢሸበሌ፣ በደናንና በጀንጋብ፣ በቆራሄ፣ በገድለጉቢ፣ በደገሀቡር፣ በሰቦበኒ፣ በጉራቴ፣ በእነሌ፣ በቢርቆድና በሌሎችም የጦር ግንባሮች የኢትዮጵያ ሠራዊት ከጠላቱ ጋር በመተናነቅ ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፈለ፡፡

ለኢትዮጵያና ለኢጣሊያ ጦርነት መንስኤ የሆነውን ይህንን አጭር ታሪክ መጥቀስና ማስታወስ የተፈለገው በኢትዮጵያና በኢጣሊያን መካከለ የተካሄደውን የጦርነትና የዲፕሎማቲክ ፍልሚያ ሙሉ ታሪክ አድርጐ ለማቅረብ ሳይሆን የኦጋዴን ሰፊ ሕዝብ በጦርነቱ ጊዜ በኢትዮጵያዊነቱ የሀገሩን ነፃነት ላለማስደፈር በየጦር ግንባሮች ያደረገውን ተጋድሎና የተጫወተውን ሚና ከብዙ በጥቂቱ ለመግለጽ ነው፡፡
የኦጋዴን ሕዝብ የኢጣሊያንን ወረራ አስመልክቶ በየጦሩ ግንባር በወታደርነትና በወዶ ዘማችነት የጠላትን ጦር በመውጋት ተዋድቋል፡፡ የኢትዮጵያ ጦር የስንቅ ችግር እንዳይደርስበት በግና ፍየሉን፣ እንደዚሁም የሥጋ ከብቱን እየነዳ ለጦሩ በማቅረብ ድጋፍ ሰጥቷል፡፡ ወደ ኦጋዴን ለዘመተው ጦር ስንቅና መሣሪያ የሚያቀብሉ የተሽከርካሪ መኪናዎች እጥረት ከፍተኛ ችግር ስለነበር ወደየጦሩ ግንባር ውሃ፣ ስንቅና መሠሪያ የሚያጓግዙ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ የጭነት ግመሎች

በማቅረብ የሎጅስቲኩን ችግር አቃልሏል፡፡ ወደ ጠላት ይዞታ መሬት በመግባት የጠላትን የጦርነት አሰላለፍና አሰፋፈር፣ የመሣሪያውን ዓይነት፣ ጥራትና ብዛት፣ ጥንቃቄውንም በመገምገም ለኢትዮጵያ ጦር ስትራቴጂ አዘገጃጀት ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች በማቅረብ ተሳትፏል፡፡ የኢትዮጵያ ጦር በጠላት ምሽጐች ላይ አደጋ ለመጣል ከሠፈሩ ወጥቶ ንቅናቄውን በሚያደርግበት ጊዜ ወይንም ስትራቴጂካዊ ማፈግፈግ ለማድረግ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ በመንገድ መሪነት ጠቃሚ አገልግሎት ሰጥቷል፡፡ ጠላት ኦጋዴንን ከያዘ በኋላ ከኢትዮጵያ ጐንተሰልፋችሁ ነበር እያለ ብዙዎቹን እየያዘ ወደ ግዞትና እስር ቤት ሲወስዳቸው ብዙዎቹ ደግሞ ውርደትን በጠላት እጅ አንቀበልም እያሉ ወደ ጅቡቲና በርበራ በመሰደድ መራራ ግፍ ተቀብለዋል፡፡

የሶማሌ አርበኞች

የጣሊያን መንግሥት በወልወል ግጭት ሳቢያ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት በአወጀበት ጊዜ ከኦጋዴን ጐሳዎች የተውጣጡ 600 ያህል የኦጋዴን ተወላጆች ጅጅጋ ላይ መጠነኛ የሆነ ወታደራዊ ትምህርት ከቀሰሙ በኋላ በወልወል ግንባር ገድለ ጉቢ በሚባለው ሥፍራ ተመድበው በቀኛዝማች አሊ ኑር መሪነት የኢጣሊያንን ጦር ፊት ለፊት በመውጋት ታላቅ ጀግንነት ፈጽመዋል፡፡ በምሥራቅ በኩል የጣሊያንን ግፊት በመቋቋም ረገድ ታላቅ ተጋድሎ ያደረጉትን ግራዝማች (በኋላ ደጃዝማች) አፈወርቅ ወልደሰማያትን ታሪክ በሚገባ ሊያስታውሳቸው ይገባል፡፡ ግራዝማች አፈወርቅ ወልደሰማያት በኦጋዴን ግንባር አዛዥ በነበሩት በደጃዝማች ነሲቡ ሥር በመሆን በቆራሄ በኩል መሽገው ጣሊያንን በሚያስደነግጥ ጀግንነት ለአንድ ዓመት ተዋግተዋል፡፡ ምሽጋቸውም የማይበገርና ጠላትን ግራ ያጋባ በመሆኑ ይህንኑ ምሽግ ለማፍረስ ጣሊያኖች ያልፈጸሙት ነገር አልነበረም፡፡ የኦጋዴን ሶማሌ አርበኞችም ግራዝማች አፈወርቅን ተከትለው ብዙ መስዋዕትነት ከፍለዋል፡፡

በመጨረሻ ግን ጣሊያን በ 60 አውሮፕላኖች አከታትሎ ምሽጉን በመደብደብ የኢትዮጵያን ሠራዊት በታተነው፡፡ ግራዝማች አፈወርቅም በዚሁ ጦርነት ላይ ቆስለው ሞቱ፡፡ ከመሞታቸው በፊት ወታደሮቻቸው(ኦጋዴኖች) ተሸክመው ወደ ሌላ ቦታ ሊወስዷቸው ሲሉ ከዚህ የሚከተለውን ተናገሩ፡፡

“እስካሁን ድረስ ከጠላት በጽኑ ተከላከልን፡፡ ባቆየነው ምሽግና እናንተ የጦር ጓደኞቼ እንደገና በምትዋጉበት መካከል አስቀምጡኝ፡፡ ስሞትም ከአውሮፕላን አደጋ ለመከላከል በተቆፈረው ጉዳጓድ ውስጥ ቅበሩኝ እንጂ አደራችሁን ከዚህ ሥፍራ ወደሌላ አትውሰዱኝ” በዚሁ ኑዛዜአቸው መሠረትም እዚያው ቆራሄ እንዲቀበሩ ተደረገ፡፡ በወቅቱም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጅጅጋ ድረስ ሄደው ስለተፈጸመው የጀግንነት ሥራ ሠራዊቱን አመስግነዋል፡፡

በገድለጉቢ ግንባር በኩል ደግሞ የእስማኤል ጉምአድሌ፣ የኢብራሂም፣ የመሣጉም አድሊና የአግዮኒስ ፡ በደገሃቡር፣ በሰሶበኒ፣ በአነለ፣ በበርቆድ ግንባር በጀግንነታቸው የታወቁት የሬር አሊና የሬር ሐሩን፣ እንዲሁም ለማለ ንጉር ጐሳዎች በጦርነቱ ወቅት ወደር የሌለው ሚና ተጫውተዋል፡፡ እነ ደጃዝማች መሐመድ ኢብራሂምና ሌሎቹም የጐሣ መሪዎች ከየጐሣዎቻቸው የመለመሏቸውን ወዶ ዘማቾች በጦሩ ግንባር አሰልፈው ከኢጣሊያን ጦር ጋር ፊት ለፊት በመግጠም፣ ጦር መሣሪያ በመማረክ ግዳይ ጥለዋል፡፡ በደገሀቡር አካባቢ በጥይት ተመትቶ ከወደቀው የጠላት አውሮፕላን ላይ ሞተው የተገኙት የኢጣሊያ ፓይለቶችን በደም ፍላት ስሜት ተገፋፍተው እንገታቸውን ከቆረጡ በኋላ ጭንቅላታቸውን በጊዜው ለነበሩት ጦር አዛዥለደጃዝማች ነሲቡ አስረክበዋል፡፡

የኢጣሊያ መንግሥስት እንደቀረው የኢትየጵያ ክፍል ሁሉ ኦጋዴንን ከ 1936 እስከ 1941 ድረስ በአስተዳደረበት ጊዜ እንደሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኦጋዴኖችም ብዙ ግፍ ተፈጽሞባቸውል፡፡ የጣሊያን መንግሥት ኦጋዴንን ከሐረር ጠቅላይ ግዛት ገንጥሎ ወደ ሶማሊያ በመደረብ በአንድነት ለማስተዳደር ባደረገው ሙከራ የኦጋዴን ሕዝብ ከመሀል ሀገር ጋር ያለው ግንኙነት ለአምስት ዓመት ተቋርጦ ነበር፡፡ የኢጣልያ ጦር ከኢትዮጵያ ተባርሮ ከወጣ በኋላ “ከጠላት የተማረኩ ሀገሮች አስተዳደር” በሚል ስያሜ ኦጋዴንን ጨምሮ በእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ሥር ወደቁ፡፡

እንግሊዞች ጅጅጋንና አካባቢውን በ 1940(እ.ኤ.አ) አስረክበው ሲወጡ የኢትዮጵያ መንግሥት ተመልሶ በአካባቢው በገባበት ጊዜ “ርስታችሁን ነጥቆ ለአማራ ይሰጥባችኋል፣ ከኢጣሊያ ይዞታ ጊዜ ጀምሮ ያለውንም የ 12 ዓመት ዕድገት ያወድምባችኋል” የሚል ሰፊ ፕሮፖጋንዳ ማሰራጨት ጀመሩ፡፡ የእንግሊዝ መንግሥት ከጅቡቲ በቀር መላው የሱማሌ ነገድ የሚኖርባቸውን ቦታዎች በቀጥታ በቁጥጥር ሥር ለማድረግ ባይችልም በዚህ አጋጣሚ በመጠቀም “ታላቋ ሶማሊያ” በሚል ስያሜ በእንግሊዝ ኮመንዌልዝ ሥር የሚተዳዳር አንድ ግዛት ለመፍጠር ምኞት አድሮበት እንደነበር የታወቀ ነው፡፡

የመጀመሪያው የሱማሊያ ህገመንግት በሰኔ ወር 1961 ሲወጣ በአንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 4 ላይ በኢትዮጵያ፣ በጅቡቲና በኬንያ የሚኖሩት የሱማልኛ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች ከሱማሊያ ጋር ወደፊት የሚዋሀዱበትን ሁኔታ የሱማሊያ መንግስት መከተል እንደሚገባው በመደንገጉ በኢትዮጵያና በሱማሊያ መካከል ለሚቀጥሉት አመታት ሰላም እንዲጠፋ ያደረገ ዋናው የሱማሊያ መንግስት የተስፋፊነት ፖሊሲ ሆነ፡፡

የዳኖት ጦርነት

ሶማሊያ ነፃ በወጣችበት በዓመቱ የሶማሊያ መንግስት በኢትዮጵያ ላይ ሰፊ ወረራ በማቀድ በዳኖት ላይ ጦርነት ከፈተ፡፡ ጊዜውም ታህሳስ 19 ቀን 1953 ነበር፡፡ እንደሚታወቀው ይህ ጊዜ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ዘወትር የሚታወስ ክንዋኔ የተፈጸመበት ወቅት ነበር፡፡ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይና ጓደኞቻቸው መፈንቀለ መንግሥት የሞከሩበት ወቅት ነው፡፡ በሶማሊያ መንግስት ግምት የኢትዮጵያ መንግሥቱ የተዳከመበትና ሠራዊቱም ሃሳቡ የተበታተነበት ወቅት ስለሆነ ለማጥቃት አመቺ ይሆናል የሚል የተሳሳተ ግምት ነበር፡፡

በሶማሊያ መንግስት በኩል"በኢትዮጵያ ውስጥ የእርስ በእርስ ጦርነት ሊጀመር ነው፡፡ በኦጋዴንም የሠፈረው ጦር በየቦታው ሊሰማራ ነው፡፡ ኦጋዴን ውስጥ ያለው ኃይል ተዳክሞ ያሉት የፖሊስ ጣቢያዎቹ ብቻ ናቸው"በሚል ዕምነት ተነስተው ዳኖት ላይ ጦርነት ከፈቱ፡፡ እውነትም ዳኖት ላይ የሠፈረው ጦር አነስተኛ ነበር፡፡ ግን በአፋጣኝ የድጋፍ ጦር ተልኮ በተደረገው የ 36 ሰዓት ጦርነት የሶማሌ ጦር ተሸንፎ ወደ መጣበት ተመለሰ፡፡

እንደገና በኢትየጵያ አቆጣጠር በ 1956 በሱማሌ ሰርጎ ገቦች አማካኝነት በቶጐውጫሌ በኩል አዲስ ጦርነት ተከፈተ፡፡ በየጦሩ ግንባር ተሠማርቶ ይዋጋ የነበረው የሶማሊያ መደበኛ ጦር ከባድ ጉዳት ደርሶበት የተረፈው ወደ ሶማሊያ ወሰን አፈገፈገ፡፡ በጄኔራል አማን አንዶም አዛዥነት፣ 3ኛ ክፍለ ጦር አማካኝነት በኢትዮጵያ ሠራዊት በኩል የተገኘው ድል ከፍተኛ ነበር፡፡ ጄኔራል አማን አንዶም ሀርጌሳ ሊገቡ ትንሽ ሲቀራቸው ነበር ግርማዊ ጃንሆይ እንዲመለሱ የአዘዙአቸው፡፡ ከዚህ በኋላ የሶማሌ መሣሪያ ሆነው የሚያገለግሉ የኢትየጵያ ሶማሌዎች ሁሉ በሶማሊያ መንግሥት ላይ ያላቸው እምነት ጠፋ፡፡ የሶማሊያ መንግሥት ሞራል በማያሻማ ሁኔታ ተንኮታኮተ፡፡ በዚሁ ወቅት ታማኝ የሆኑ የኦጋዴን ባላባቶች ሠራዊት በመመልመል በወዶዘማችነት በቀብሪደሐር፣ በደገሀቡርና በቀላፎ አውራጃዎች የሚተዳደሩ የሬር አብዳሊ፣ የሬር ኢስሀቅ፣ የባህጊሬ ጐሳዎች በአውራጃቸው ሾልከው የገባውን የሶማሊያ ሠርጐ ገብ ተዋግተው ደምስሰውታል፡፡

በዚሁ ጦርነት ምክንያት ከ 1956 ጀምሮ እስከ 1964 ድረስ በኦጋዴን ውስጥ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታወጀ፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ አንዳንድ አነስተኛ ግጭቶች ቢኖሩም በአጠቃላይ ኦጋዴን ሠላም ሰፈነበት፡፡

ከ 1964 እስከ 1966 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በኦጋዴን ከባድ ድርቅ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ አብዮት በፈነዳበት በ 1966 የኦጋዴን ህዝብ ከባድ ችግር ላይ ነበር፡፡ በዚህም የችግር ወቅት የዕርዳታማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር በመሆን፣ በኦጋዴን ውስጥ በተለያየ ቦታ በመዘዋወር ከዕለት እርዳታ ባሻገር የኦጋዴን ሕዝብ በጐዴ፣ በተለይም በዋቢሸበሌ ሸለቆ የሚሰፍርበትን፣ ከዘላንነት ሕይወት የሚላቀቅበትን ሁኔታ በማጥናትና ፕሮግራሙንም በተግባር ለመቶርጐም ከጓደኞቼጋ ብዙ ሙከራ አድርገናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በጐዴ አካባቢ በፋፈም ሸለቆ ሰፋፊ የእርሻ ቦታዎች በማቋቋም ለሕዝቡ ሥራ ለመፍጠርና የሠፈራንም ጥቅም ለማስረዳት ትምህርት ተሰጥቷል፡፡ ከ 150 ሺ በላይ የሚሆኑ ሶማሌዎችን ከመጠለያ አውጥቶ በቋሚነት ለማስፈር ተሞክሯል፡፡

የሶማሌ ተስፋፊዎች

የሶማሊያ ገዢዎች የጐረቤት ሀገሮችን የግዛት አንድነት የመዳፈር አላማ ሶማሊያ ራሷ አባል ሆና በምትገኝበት በአረብ ሊግ ውስጥ በሚገኙ በአንዳንድ የአረብ መንግሥታት ዘንድ የሞራል ድጋፍ ያገኘ ቢሆንም በተባበሩት መንግሥታት፣ በአፍሪካ አንድነትና በገለልተኛ መንግሥታት ድርጅቶች ዘንድ ተቀባይነት በማጣቱ የዲፕሎማሲያዊና ዓለም አቀፋዊው ዘመቻቸው የጠበቁትን ውጤት አላስገኘላቸውም፡፡ ስለሆነም የዓለምን ሕዝብ አስተያየትና ዝንባሌ በሌላ አቅጣጫ ለመሳብ የኦጋዴንን ሕዝብ ለትጥቅ ትግል ከማዘጋጀትና ከመቀስቀስ የተሻለ አማራጭእንደሌላቸው ገመቱ፡፡ በዚህም ምክንያት በሞቃዲሾው ከተማ መጀመሪያ በኦጋዴን ነፃ አውጪ ድርጅት ስም የታወቀውን፣ በኋላ ግን ከሐረርጌ ውጭ ያሉትን የሶማሊኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑትንሶማሌዎችና እንደዚሁም የተወሰኑ የሐረርጌ፣ የባሌና የሲዳሞን ኦሮሞዎች(ሶማሌ አቦ የሚሏቸውን) በመጨመር የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ግንባር የተሰኘውን የፓለቲካ ፅ/ቤትና ወታደራዊ ድርጅት እንዲቋቋም አደረጉ፡፡

በተከታታይም "የኢትዮጵያ ቅኝ ገዥነት" ለዓለም ለማሳመን ለፓለቲካ ዘመቻችን ጠቃሚ ሚና አለው ብለው በመገመት ሌላ የውጊያ ግንባር ከፈቱ፡፡ የኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባር የተሰኘውን የፓለቲካ ፅ/ቤትም እንዲከፈት አደረጉ፡፡ በነዚህም ድርጅቶች ስም በመጠቀም ኢትዮጵያ ኦጋዴንን እና ኤርትራን እስካልመለሰች ጊዜ ድረስ በአፍሪካ ውስጥ ከሚታወቁት ኮሎኒያሊስቶች ከፖርቹጋል፣ ከደቡብ አፍሪካ እና ሮዴዢያ የምትለይበት ሁኔታ የለም በማለት የፖለቲካና የፕሮፖጋንዳ ዘመቻቸውን ቀጠሉ፡፡

በአፍሪካ ውስጥ የቅኝ አገዛዝ ሥር ያሉትን የነፃነት ታጋዮች የዓለም ህብረተሰብ ለመርዳት እንደተነሳሳ ሁሉ እኛም የኦጋዴን ሶማሌዎች ታጋዮችን መርዳት አለማቀፋዊ ግዴታው ነው የሚል አቋም ያዙ፡፡ ወደ ኡጋዴንም እየገቡ ፀጥታ እንዲያውኩ ለአያሌ ወንበዴዎች ወታደራዊ ትምህርት በመስጠት ብሎም ዘመናዊ መሳሪያም በማስታጠቅ እዚያም እዚህም እየተነኮሱ በኡጋዴን ውስጥ ማቋረጫ የሌለውን ጠብ ይጭሩ ጀመር፡፡ በዚያው መጠን በሰውና በንብረት ላይ ከፍ ያለ ጥፋትና ጉዳት አደረሱ፡፡

1966 የተቀሰቀሰውን አብዮት ተከትሎ ኢትዮጵያ በፖለቲካ ትርምስ በወደቀችበት ጊዜ ሶማሌ በፀረ አብዮት ኃይሎችና በሌላ አቅጣጫ ከኤርትራ የመገንጠል እንቅስቃሴዎች እየተረዳች ኢጋጣሚውን በመጠቀም በ 1969 ኢትዮጵያ ላይ ሰፊ ወረራ ከፍታ በኦጋዴን ላይ ጊዚያዊ ድል አጋጠማት፡፡ ለሰባት ወራትም ኦጋዴንን ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጠረች፡፡ በመጋቢት 1970 የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ በከፈተው የመልሶ ማጥቃት በከፍተኛ መስዋእትነት ኢጋዴንን ሙሉ ለሙሉ ለማስመለስ ቻለ።
ዛሬ ሶማሊያ ተዳከማለች፡፡ ዚያድባሬ ለአገዛዙ እንዲያመቸው ብሎ በፈጠረው የዘር (ክላን) ልዩነት ውጥረቱ እንዳለ ነው፡፡ ሶማሊያ ከባድ የሆነ ዕልቂትና የፖለቲካ ትርምስ ውስጥ ከገባች አመታት ተቆጥረዋል፡፡ ህዝቦቿ በመጀመሪያ የፈለሱት ወደ ኢትዮጵያ ነው ኢትዮጵያም እጇቿን ዘርግታ ተቀብላቸዋለች፡፡ ያለፓስፖርትና ያለብዙ ጥያቄ እንደልብ ገብተው በሰላም የሚኖሩባት፣የሚሰሩባት ፣ አንዳንዶቹም የከበሩባት አገር በመሆኗ ብዙ ሶማሌዎች ስለኢትዮጵያ ያላቸውን አስተያየት እንዲለውጡ አስገድዷቸዋል፡፡

ምንም እንኳን ሶማሊያ የጠነከረ ማዕከላዊ መንግስት ባይኖራትም የተለያዩ መሪዎችና የፓለቲካ ሰዎች በግልጽ እንደሚናገሩት ዛሬም የታላቋ ሶማሊያ ሀሳባቸውን የሚለውጡበት ጊዜ አልተቃረበም፡፡ ካሉት ሌሎች ጂኦ ፓለቲካና ከአልሸባባብ ንቅናቄ ጋር አብሮ ሲታይ የሶማሊያ የመስፋፋት ምኞት ያለና የሚኖር የኢትዮጵያ ስጋት ነው፡፡
ዝርዝሩ ክህደት በደም መሬት የሚለው መፅሀፌ ውስጥ ይገኛል::
የኢትዮጵያ ታሪክ ምሁራን ደግሞ ይጨምሩበት::